# የመጽሐፍ ፡ ክለሳ ፤

## ሎይድ ፤ የሕግ ፡ ፍልስፍና ፡ መግቢያ ፡

(ሁለተኛ ፡ እትም ፡ ስቴቨንስ ፡ ሎንደን ፡ ፲፱፻፷፭ ፡ ዓ፡ ም፡)

በአር ፡ ኤም ፡ ከሚንግስ ፡ ተከለሰ ፡*

ይህ ፡ በለንደን ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሕግ ፡ ፍልስፍና ፡ መምህር ፡ የሆኑት ፡ የፕሮፌሰር ፡ ሎይድ ፡ መጽሐፍ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ፡፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ለወጣው ፡ መጽሐፍ ፡ ሁለተኛ ፡ እትም ፡ ነው ። ይህ ፡ እትምና ፡ በመጀመሪያው ፡ እትም ፤ ጸሐፊው ፡ እንደገለጹት ፡ «የታቀዱት ፡ የመማሪያ ፡ መጽሐፍ ፡ እንዲሆኑ ፡ ሲሆን ፡ መጽሐፉም ፡ ከታላላቅ ፡ የሕግ ፡ አዋቂዎች ፡ ጽሑፎች ፡ የተመረጡ ፡ ፅንሰ-ሀሳቦችን ፡ የያዘ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ለብዙዎቹ ፡ የመጽሐፉ ፡ ክፍሎች ፡ በቂ ፡ መግለጫዎች ፡ በመግቢያ ፡ ምዕራፎች ፡ መልክ ፡ ስለተጻፉና ፡ ጽሑፎቹ ፡ ሁሉ ፡ የተሟላ ፡ ማብራሪያ ፡ ስላላቸው፡ ተማሪውን ፡ ከነዚህ ፡ ፅንሰ-ሀሳቦች ፡ በይበልጥ ፡ ሊያስተዋውቀው ፡ ይችላል ።»

ከሕግ ፡ ፍልስፍና ፡ (ቃሉን ፡ እንግሊዛውያንና ፡ አሜሪካውያን ፡ በሚጠቀሙበት ፡ ዓይነት)፡ የተላመደ ፡ ማንኛውም ፡ አንባቢ ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በወጠነው ፡ ዓላማ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደተሳካለት ፡ ሳይገረም ፡ አይቀርም ። ምንም ፡ እንኳ ፡ ሁሉን ፡ አጠቃላይ ፡ እንዲሆኑ ፡ ባይታሰብም ፡ ተማሪው ፡ አሥር ፡ መሠረታውያን ፡ አርዕስተ-ትምህርቶችን ፡ ያገኛል ። ለጥናት ፡ የተመረጡት ፡ ክፍሎች ፡ በጣም ፡ አግባብ ፡ ያላቸው ፡ ሲሆኑ ፡ እነዚህም ፤ የሕግ ፡ ፍልስፍና ፡ ጠባይ ፡ የሕግ ፡ ትርጉም ፡ የተፈጥሮ ፡ ሕግ ፤ ፍጹም ፡ ንጹሕ ፡ የሆነ ፡ የሕግ ፡ ፅንሰ-ሀሳብ ፡ (Pure theory of law) ፤ የበላይነትና ፡ ኢምፔራቲቭ ፡ ቲዮሪ ፡ አፍ ፡ አናሊቲካል ፡ ፖስቲቪዝም ፤ የሕግ ፡ ምንጭ ፡ የኅብረተ ፡ ሰቡ ፡ አኗኗር ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ ክፍል ፡ (Sociological School) የአሜሪካን ፡ ሪያሊዝም ፤ የስካንዴኔቪያን ፡ ሪያሊስቶች ፤ ሕግ ፡ ከልማድና ፡ ከታሪክ ፡ የሚመነጭ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ ክፍልና ፡ (custom and the historical school) የሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ናቸው ። የተመረጡት ፡ ደራሲያን ፡ ከታላላቆች ፡ ግሪኮች ፡ ጀምሮ ፡ እስካሁኖቹ ፡ ሊቃውንት ፡ ድረስ ፡ እንደትልቅነታቸውና ፡ የአገላለጽ ፡ ችሎታቸው ፡ ነው ፤ የፍልስፍና ፡ ሀሳቦችን ፡ ለማብራራት ፡ ያህል ፡ ፍርዶች ፡ መጠቀሳቸው ፡ አስፈላጊ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ከሚያስፈልገው ፡ በላይ ፡ አለመጠቀሳቸው ፡ የሚያስደስት ፡ ነው ፤ (በሕግ ፡ ፍልስፍና ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ ፍርዶችን ፡ ማብዛት ፡ ዋናዎቹ ፡ የፅንሰ-ሀሳብ ፡ ጭብጦች ፡ ለማብራሪያ ፡ በሚቀርቡ ፡ ፍርዶች ፡ እንዲዋጡ ፡ የማድረግ ፡ ጉዳት ፡ ያመጣል) ። ፕሮፌሰር ፡ ሎይድ ፡ ፈላስፋ ፡ እንደመሆናቸው ፡ መጠን ፡ የግል ፡ አስተያየታቸውን ፡ ያሰፈሩባቸው ፡ መግለጫዎች ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ከመሆናቸውም ፡ በላይ ፡ በቦታቸው ፡ የገቡ ፡ ለመሆናቸው ፡ አያጠራጥርም ።

ባጭሩ ፡ መጽሐፉ ፡ የሚደነቅ ፡ ነው ፤ በተለይም ፡ በሕግ ፡ ፍልስፍና ፡ ትምህርት፡ መምህሩ ፡ በአንድ ፡ መማሪያ ፡ መጽሐፍ ፡ ብቻ ፡ ለመጠቀም ፡ ከፈለገ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ መገልገሉ ፡ በጣም ፡ ይረዳል ።

* ቀደም ፡ ብለው ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ በሕግ ፡ ፋክልቲ ፡ አባል ፡ ነበሩ ።

ለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በተመረጡት ፡ ጽሑፎችና ፡ ጸሐፊዎች ፡ አቃቂር ፡ ማውጣት ፡ አይቻልም ። የደራሲው ፡ ችሎታ ፡ ከፍተኛ ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ያደረጉት ፡ ምርጫ ፡ ለግላዊ ፡ የአእምሮ ፡ ግምታቸው ፡ የተተወ ፡ ነው ። ለጥናት ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ፡ ማንኛውም ፡ ያልተጠቀሰ ፡ ነገር ፡ መተኪያ ፡ ሊደረግለት ፡ ይቻላል ። በእርግጥም ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሎይድ ፡ እንደገለጹት ፡ በመጀመሪያው ፡ እትም ፡ ላይ ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮች፡ ሆን ፡ ብለው ፡ ሳይጠቅሱ ፡ ያለፏቸው ፡ ስላሉ ፡ እነዚህን ፡ አርዕስተ-ትምህርቶች ፡ ለመከታተል ፡ ለሚፈልግ ፡ ሁሉ ፡ የሚነበቡ ፡ መጻሕፍት ፡ ዝርዝር ፡ ሰጥተዋል ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ የሶሻሊስትን ፡ የሕግ ፡ ፅንስ-ሀሳብ ፡ ከሁለተኛው ፡ እትም ፡ ውስጥ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሎይድ ፡ ያስቀሩበት ፡ ምክንያት ፡ አጥጋቢ ፡ ቢሆ ንም ፡ ተቺው ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ቢብራራ ፡ ይወድ ፡ ነበር ። ወደ ፡ ኮምፓራ ቲቭ ፡ ሕግና ፡ የሶቪየት ፡ ቅንጅት ፡ ገለጻ ፡ ስንገባ ፡ (ይህ ፡ ችግር ፡ የአሜሪካን ፡ ሪያሊ ዝምንና ፡ የስካንዴኔቪያን ፡ አስተሳሰብ ፡ ደጋፊዎችን ፡ ስናጠና ፡ መምጣቱ ፡ አይቀር ም) ፡ የማርክስንና ፡ የኤንግልስን ፡ አስተሳሰብ ፤ ይኸውም ፡ ሕግን ፡ ከነጭራሹ ፡ ስለ ማጥፋት ፡ አስተያየት ፡ ቢሰጥበት ፡ኖሮ ፡ መጽሐፉ ፡ በይበልጥ ፡ የተሟላ ፡ ይሆን ፡ ነበር ። ኬልስንን ፡ በመጥቀስና ፡ የቅጣትን ፡ አስፈላጊነት ፡ በመግለጽ ፡ የ፲፱ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ፈላስፋዎች ፡ ስለ ፡ ኅብረተ-ሰብ ፡ አቋም ፡ ለውጥ ፡ ያቀረቧቸውን ፡ ችግሮች ፡ በሚገባ ፡ መቋቋም ፡ አይቻልም ። ተቺው ፡ አፍሪቃ ፡ ውስጥ ፡ ባስተማሪነት፡ ባገኘው ፡ ዕውቀት ፡ በሕግ ፡ የሶሻሊዝምን ፡ አከራካሪ ፡ ጉዳዮች ፡ በደንብ ፡ መግለጽ ፡ እንደሚያስፈልግና ፡ ዝቅ ፡ ተደርገው ፡ መታየትም ፡ የሌለባቸው ፡ መሆኑን ፡ ለመረዳት ችሏል ።

የሕግ ፡ የበላይነት ፡ አስተሳሰብ ፡ ከመቼውም፡ይልቅ ፡ በጣም ፡ አጠራጣሪ ፡ (አስጊ) ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ ስላለ ፡ የሕግ ፡ ፍልስፍና ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ከፍተኛ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ ነው ። ፕሮፌሰር ፡ ሎይድ ፡ በተፈጥሮ ፡ ሕግና ፡ መንግሥት ፡ በሚደነግገው ፡ ሕግ ፡ መካ ከል ፡ ያለውን ፡ ግጭት ፡ በአንክሮ ፡ በመመልከት ፡ አንዱ ፡ የአስተሳሰብ ፡ ክፍል ፡ ከሌ ላው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጥቅም ፡ ለማግኘት ፡ እንደሚችል ፡ ለመረዳት ፡ በሚያስችል ፡ ጽ ሑፍ ፡ አቅርበውልናል ። በእርግጥም ፡ የዊትግንስቴን ፡ መግቢያ ፡ የግጭቱን ፡ መሠረት ፡ የቋንቋ ፡ ችግሮች ፡ ለመረዳት ፡ በጣም ፡ ይጠቅመናል ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሕግ ፡ ፍል ስፍናዎችን ፡ መጋጨት ፡ በአንክሮ ፡ የመመልከት ፡ ጉዳይ ፡ ሕግን ፡ አውቆ ፡ መቀበ ልን ፡ ስለሚጠይቅ ፡ ሕግን ፡ ለመቃወም ፡ ምክንያት ፡ አይገኝም ። ማርክስ ፡ ጸረ-ሕግ ፡ ስለሆነ ፡ ተለይቶ ፡ መጠናት ፡ አለበት ፡ ማለት ፡ ኒቼ ፡ "ጸረ-ክርስቶስ ፡" ስለነበር ፡ ከሃይማኖት ፡ ፍልስፍና ፡ ውጭ ፡ መጠናት ፡ አለበት ፡ እንደማለት ፡ ያህል ፡ ነው ።

የማርክስ ፡ የንቅናቄ ፡ አስተሳሰብ ፡ ደጋፊ ፡ የሆኑት ፡ የማርኩስ ፡ ጽሑፎች ፡ በዛሬ ፡ ጊዜ ፡ በተማሪዎች ፡ ዘንድ ፡ በጣም ፡ ተደናቂነት ፡ ስላላቸውና ፡ የንቅናቄም ፡ (ሪቮልዩ ሽን) ፡ አስፈላጊነት ፡ እየጠነከረ ፡ ስለሄደ ፡ በሕግ ፡ ፍልስፍና ፡ ውስጥ ፡ የጸረ-ሕግ ፡ ፅንስ-ሀሳቦች ፡ በደንብ ፡ መጠናት ፡ ያስፈልጋቸዋል ። ያሁኑ ፡ ይዞታ ፡ ከቀጠለ ፡ ግን ፡ በሃይማኖት ፡ በኩል ፡ "እግዚአብሔር ፡ ሞቷል ፡" የሚለው ፡ ዋና ፡ አሳሳቢ ፡ ጉዳይ ፡ እንደሆነ ፡ ሁሉ ፡ በሕግ ፡ ፍልስፍናም ፡ "ሕግ ፡ ሞቷል ፡" የሚለው ፡ ዋናው ፡ አሳሳቢ ፡ ጉዳይ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

ይህ ፡ ለምን ፡ ሆነ ? ለዚህ ፡ ጉልህ ፡ ምክንያት ፡ በመንግሥት ፡ የተደነገገው ፡ ሕግ ፡ ጥናት ፡ የፍትሕን ፡ ጉዳይ ፡ ገሸሽ ፡ ስላደረገው ፡ ነው ። በተለይም ፡ አከፋፋይ ፡ ፍትሕን ፡ ወይንም ፡ በኅብረተ-ሰብ ፡ ውስጥ ፡ ጥቅምንና ፡ ግዴታን ፡ ባልተዛባ ፡ ተመጣጣኝነት፡ ለማዳረስ ፡ የሚጠቅመው ፡ መምሪያ ፡ በቀላሉ ፡ ከተፈጥሮ ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ ሊማታ ፡ ይች ላል ፤ ግን ፡ ሁለቱ ፡ አንድ ፡ አይደሉም ። ዋናው ፡ ጉዳይ ፡ ኃይል ፡ አንዳንድ ፡ ግቦችን ፡

ማስፈጸሚያ ፡ ዘዴ ፡ መሆኑን ፡ አያሌ ፡ ሰዎች ፡ ከመቅጽበት ፡ መረዳታቸው ፡ ነው ። የተፈጥሮ ፡ ሕግ ፡ የትኞቹ ፡ ቀዋሚ ፡ ሀሳቦች ፡ ትክክለኛ ፡ ወይም ፡ ውሸት ፡ መሆናቸውን ፡ ለመወሰን ፡ በምክንያታዊ ፡ አስተሳሰብ ፡ ሲጠቀም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በመጨረሻ ፡ በስሜት ፡ መመራትን ፡ ለማስወገድ ፡ ባይቻልም ፡ (ፈላስፋው ፡ ሕዩም ፡ ፍትሕ ፡ ስሜት ፡ መሆኑን ፡ ያስተምረናል) ፡ ጊዜያዊውን ፡ የኅብረተ ፡ሰብ ፡ አቋም ፡ የሚያረጋግጥ ፡ የአእምሮ ፡ ምርምር ፡ ወይም ፡ ስሜታዊ ፡ ዘዴ ፡ ስለሌለ ፡ ኃይል ፡ ማረጋገጫ ፡ ዘዴ ፡ ይሆናል ። ከርከጋርድ ፡ ለእምነት ፡ ሲባል ፡ የመሞትን ፡ ፈቃደኝነት ፡ ለዚያ ፡ እምነት ፡ ትክክለኛነት ፡ ማስረጃ ፡ አድርጎ ፡ ይቀበለዋል ። ደግሞም ፡ ሕይወትን ፡ የማሳለፍ ፡ በጐ ፡ ፈቃድ ፡ ጽኑ ፡ ተጋዳዮችን ፡ ይፈጥራል ። ባጭሩ ፡ ማርክስ ፡ ከርከጋርድና ፡ ማርኩስ ፡ ባንድነት ፡ ለሕግ ፡ የበላይነት ፡ ብርቱ ፡ ተቃዋሚዎች ፡ ሆነዋል ። ምናልባት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ሎይድ ፡ ከፍተኛ ፡ ዕውቀታቸውን ፡ እነዚህ ፡ ጸረ-ሕግ ፡ ደራሲያን ፤ የኃይል ፡ ተጋድሎ ፡ የዘወትር ፡ ተግባር ፡ በሆነበትና ፡ ሕግ ፡ በጠቅላላው ፡ ለኅብረተ-ሰብ ፡ የመሻሻል ፡ እርምጃ ፡ እንቅፋት ፡ ሆኖ ፡ በሚታይበት ፡ ዓለም ፡ የፈጠሯቸውን ፡ ችግሮች ፡ ለመተንተን ፡ እንደሚጠቀሙበት ፡ ተስፋ ፡ ይደረጋል ። አውስቲን ፡ ለሕግ ፡ መታዘዝ ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ የሚያቀርበው ፡ ሀሳብ ፡ እውነት ፡ ከሆነ ፡ ይህንን ፡ ልማድ ፡ በመተው ፡ ላይ ፡ ነን ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። የሕግ ፡ ልማድን ፡ ለማስቀረት ፡ የሚረዱንን ፡ ሰዎች ፡ አስተሳሰብ ፡ ከመመርመር ፡ ይበልጥ ፡ ለሕግ ፡ ፍልስፍና ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ዐቢይ ፡ ጉዳይ ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ?